## ስለ ቤተሰብ አገልግሎት ተጨማሪ ጉዳዮች

የክርስቲያን ቤተሰብ አገልግሎት፣ በኤድስ ወረርሽኝ በመሠቃየት ላይ ላለው አፍሪካ፣ ተስፋን እየፈነጠቀ ነው:: የትምህርት ሥራ ዘወትር ጊዜን ይጠይቃል፤ ነገር ግን ጊዜ ወስዶ ሲሠራ ደግሞ ውጤቱ ያምራል:: ስለዚህ አብያተ ክርስቲያናት ተሞክሮዎቻቸውን የማካፈልና ያገኙዋቸውን አዳዲስ የሥራ ውጤቶችና የሥራ ዓይነቶች በተግባር ላይ የማዋል ዕድል አላቸው::



በአሠልጣኞች ሥልጠና ላይ ትምህርት ሲሰጥ

የኢትዮጵያ ወ/ቤ/ክ መካነ ኢየሱስ፣ የቤተሰብ አገልግሎት (የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት ፕሮግራም) ዓላማ ምእመናን በትዳራቸውና በቤተሰባቸው ውስጥ ደስተኞች ሆነው እንዲኖሩ ማገዝ ነው:: ባልና ሚስቶች ደስተኞች በሆኑ ቊጥር፣ በየተሰማሩበት ሥራ የበለጠ የተቃና አገልግሎት መስጠት ይችላሉ::

በመጨረሻም የመርሐ ግብሩ ወይም የፕሮግራሙ ግብ የቤተሰብ አገልግሎትን ከቤተ ክርስቲያን የትምህርት ዓይነቶች ጋር አቀናጅቶ በመደበኛነት መስጠት ነው::

### ድጋፋችሁ ያስፈልጋል

እንደ ፕሮግራም የቤተሰብ አገልግሎት በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ አዲስ ነው:: ይህን ሥራ ለማደራጀት ሊገኝ የሚችል የሀብት ምንጭ ሁሉ ተቀባይነት አለው:: እባካችሁ ለቤተሰብ አገልግሎት ጸልዩ፣ በልዩ ልዩ መንገድም ደግፉት፣ ድጋፋችሁ እንደ ገንዘብ መለገስም ሆነ በተግባራዊ ሁኔታ መርዳትም ይሁን:: እጅ ለእጅ ተያይዘን ጌታን በዚህ መስክ እናገልግል !

(በታኅሣሥ ወር 2001 ዓ. መ. የተሻሻለ)

## የመገናኛ አድራሻዎች:-


የኢትዮጵያ
ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን
መካነ ኢየሱስ

የወንጌል ማዳረስና የቴኦሎጊ መምሪያ

**የቤተሰብ**
**አገልግሎት**

የቤተሰብ ሕይወት
ትምህርት ፕሮግራም

**✉ ፖ.ሳ.ቁ 2087**
**አዲስ አበባ ኢትዮጵያ**

☏ 0115 50 78 46
(የመምሪያው ቢሮ)

**e-mail:** family@eecmy.org
**Internet:** http://www.eecmy.org/




የቤተሰብ አገልግሎት የሥራ ቡድን በ2001 ዓ.ም.

የኢትዮጵያ
ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን
መካነ ኢየሱስ



# የቤተሰብ አገልግሎት

## የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት ፕሮግራም

**2001 ዓ.ም.**

## ሠራ መሠረት

የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ  በፍጥነት በማደግ ላይ የምትገኝ አፍሪቃዊት ቤተ ክርስቲያን ናት፡፡ የአባላት ብዛት (በ1951 ዓ.ም. ቤተ ክርስቲያኒቱ በተመሠረተችበት ጊዜ) 20.000 የነበረ ሲሆን፣  በ2001 ዓ.ም. ቤተ ክርስቲያኒቱ 50ኛ ዓመትዋን (ኢዮቤልዩን) ስታከብር ከአምስት ሚሊዮን  በላይ ሆኖአል፡፡ ቤተ ክርስቲያኒቱ ዓላማዋ ወንጌልን ለማስፋፋት በመሆኑ፣ በብዛት በወንጌል ማዳረስ ላይ ታተኩራለች፡፡ ሆኖም ዕድገትዋ ፍጥነት  ቢያሳይም፣ ነባር ምእመናንን በሚገባ ደግሞ በወንጌል መመገብና ማሳደግ  ይጠበቅባታል፡፡ ባለፉት   ዓመታት  በግልጽ የተረሳው ሥራ የጋብቻና የቤተሰብ እንክብካቤ ነበር፡፡

## ስለ ቤተሰብ አገልግሎት መስፋፋት

ከ1992 ዓ.ም. ጀምሮ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን መካነ ኢየሱስ  ለቤተሰብ አገልግሎት ልዩ የሆነ ፕሮግራም ታካሄዳለች፡፡ ባሁኑ ጊዜ ይህ ፕሮግራም በዋናዋ ቤተ ክርስቲያን የወንጌል ማዳረስና ቴኦሎጊ መምሪያ ሥር ነው፡፡ **የቤተሰብ አገልግሎት አምስቱ ዋና ክፍሎች**:- 1) ቅድመ ጋብቻ ትምህርት፣ 2) ድኅረ ጋብቻ ትምህርት፣ 3) ልዩ ልዩ  ቡድኖችን ስለ ጋብቻና ቤተሰብ ማስተማር፣ 4) የጋብቻና የቤተሰብ ምክር አገልግሎትና 5) ለቤተሰብ አገልግሎት ሥልጠና ማዘጋጀት ናቸው፡፡

የቤተሰብ አገልግሎት በዋና መ/ቤት ያሉ ሠራተኞች ወ/ሮ አበራሽ ቶሌሣና ቄስ ገነቲ ዋዩሣ (የሥራው አስተባባሪ)፣ እና በፊንላንድ ወንጌላዊት ሉተራን ሚስዮን (FELM) የተላኩ፣ የሥራው አማካሪዎች ሲ/ር አና ካሪና  ፓልሙና ቄስ ማቲ ፓልሙ ናቸው፡፡ የዚህ ፕሮግራም ባጀትን የሰጠው የፊንላንድ ወንጌላዊት ሉተራን ሚስዮን ነው፡፡

ቅድመ ጋብቻ ትምህርት ምዕራብ ኢትዮጵያ ባሉ  ሲኖዶሶች በፊንላንድ ሉተራን ሚስዮን (FLM) በተላኩ፣ በሲ/ር ሄሌና ረይሰኔንና በሚ/ር ታፒዮ ረይሰኔን አማካይነት እየተዘጋጀ ነው፡፡

## መሠረት፣ ዓላማዎችና ግቦች

የመካነ ኢየሱስ የቤተሰብ አገልግሎት **የተመሠረተው፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ ነው፡፡**

**ከፕሮግራሙ ዓላማዎች መካከል ጥቂቶቹ:-**

- የቤተሰብ  አገልግሎትን  በተመለከተ፣  በመሪዎች  ዘንድ ተፈላጊው ግንዛቤ  እንዲኖር  ማድረግ፣
- የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮችን ለዚህ አገልግሎት ማሠልጠን፣
- የጋብቻ  ትምህርቶችን፤  መዝናኛን  ያካተቱ  የውይይት መድረኮችን ወዘተ. ማዘጋጀት፣
- የጋብቻና  ቤተሰብ  ምክር  አገልግሎትንና  የዚህ  አገልግሎት መዋቅሮችን ማጠናከር፡፡
- ለቤተሰብ አገልግሎት የሚጠቅሙ የትምህርት መሣሪያዎችን ማዘጋጀትና መሰብሰብ፡፡

**የፕሮግራሙ ግብ በተቻለ መጠን አሠልጣኞችን በብዙ ማዘጋጀት ነው፡፡** እነዚህ ሰዎች የቤተሰብ አገልግሎት አስተማሪዎች ሆነው ማገልገል ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሚያገለግሉትም በየተመደቡበት ሥራ ላይ ሆነው ነው፡፡

## ዓላማ የተደረገባቸው ስፍራዎች:- መላዋ ቤተ ክርስቲያን

የቤተሰብ አገልግሎት መርሐ ግብር የትኩረት ስፍራዎች የቤተ ክርስቲያን ክፍሎች በሙሉ (20 ሲኖዶሶችና አዲስ የሥራ ክፍሎች) ናቸው፡፡ በአራት የት/መለኮት ሰሚናሪዮሞችና በመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤቶች ወደፊት የመንግሥት ት/ቤቶችም በመርሐ ግብሩ ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ ሌሎችም በመርሐ ግብሩ  ውስጥ የሚጠቃለሉ ቡድኖች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ሥራውን ስለማስፋፋት በምንናገርበት ጊዜ ወሳኙ ነገር የየአካባቢ አስተማሪዎችን የማሠልጠኑ ጉዳይ ነው፡፡



በሥልጠና ጊዜ ለወጣቶች የቅድመ ጋብቻ ትምህርትን የመስጠት ልምምድ

በመጀመሪያ ዓመታት ፕሮግራሙ በቤተ ክርስቲያኒቱ ሲኖዶሶች ሁሉና በዋናው ጽ/ቤት መሠረታዊ የጋብቻ ኮርስ አዘጋጅቶአል፡፡ በኢትዮጵያ ወ/ቤ/ክ መካነ ኢየሱስ የትምህርተ መለኮት ተቋማት ላሉ ተማሪዎች ሁሉ  መሠረታዊው የቤተሰብ አገልግሎት ኮርስን እየተማሩ ናቸው፡፡

**ለቤተሰብ አገልግሎት የአሠልጣኞች ኮርሶች** እየተሰጡ ናቸው፡፡ ዓላማውም፣ ኢትዮጵያውያን ባልና ሚስቶችን ለዚህ አገልግሎት በየአከባቢያቸው መሠረታዊ የጋብቻ ትምህርት እንዲሰጡ ለማሠልጠን ነው፡፡ በነሐሴ 2000 ዓ.ም. ይህንን የቤተሰብ አገልግሎት ሥልጠና ኮ ርስ የፈጸሙ 374 ሰዎች ነበሩ፡፡ ይህን ኮርስ ከፈጸሙ  በኋላ የሚያስተምሩት በሲኖዶስ ደረጃ ብቻ ሳይሆን  በሰበካና በማኅበረ ምዕ መናን ደረጃ ሲሆን ትምህርቱን የሚሰጡት በአካባቢው ቋንቋ ነው፡፡

ከእነዚህ ሰዎች መካከል 34 **የቤተሰብ አገልግሎት የአሠልጣኞች አሰልጣኞች** ትምህርቱን ተከታትለዋል፡፡ እነርሱ ወደፊት የአሠልጣኞች  ኮርሶችን በየሲኖዶሱ እንዲያዘጋጁ ነው፡፡ ግቡ፤ ለያንዳንዱ የ10 ማ/ምእመናን ቡድን አንድ የቤተሰብ አገልግሎት አሠልጣኝ እንዲኖር ነው፡፡ **የጋብቻና የቤተሰብ አማካሪዎች ሥልጠና፤ እንዲሁም ደግሞ የወጣቶች የቅድመ ጋብቻ ትምህርት የአሠልጣኞች ሥልጠና** በ2000 ዓ.ም. ተጀምረዋል፡፡

## የቤተሰብ አገልግሎት ራእይ

- ደስታ የሰፈነበትና ጤናማ የሆነ ትዳርንና ቤተሰብን መሠረት አድርገው ጤናማ ማኅበር ምእመናንና ኅብረተሰብን ለመገንባት:-
- በትዳራቸው ደስተኞች የሆኑትን  አገልጋዮች በሕይወት ምስክርነታቸውና በትምህርታቸው አማካይነት ወንጌልን እንዲያስፋፉ ለማድረግ:-
- የክርስቲያን የቤተሰብ ሕይወትን በማጠናከር የልጃገረዶችንና የሴቶችን ደረጃ ለማሻሻል:-
- በዚህ አስፈሪ በሆነ የኤድስ ወረርሽኝ ጊዜ፣ በባልና ሚስቶች፣ በቤተሰቦቻቸው መካከል የመተማመን ሁኔታ እንዲኖር፣ የመተማመንን ጥቅም አጥብቆ በማስረዳት ለማገዝ:-
- ቅድመ ጋብቻ ትምህርትን በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከት በወሲብ ዙሪያ፣ ማለትም ከጋብቻ በፊት መታቀብና በጋብቻ ጊዜ ለአንድ የትዳር ጓደኛ ታማኝ መሆንን ለማስተማር:-
- በማኅበራነ ምእመናን ለሚካሄዱ የጋብቻና የቤተሰብ የምክር አገልግሎት ተግባራት መዋቅሮችን ለማጠናከር፡፡

## «የቤተሰብ አገልግሎት» ምንድን ነው?

በኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ዘንድ ማንኛውም ሰው በቅርብም ሆነ ዘግይቶ አንድ ቀን እንደሚያገባ / እንደምታገባ ማሰቡ የተለመደ ነው፡፡ በዚህ አገር የወንደ ላጤነት ወይም የሴተ ላጤነት ሕይወት አሳብ እንደ እንግዳ ነገር ይታያል፡፡ እንግዲህ የቤተሰብ አገልግሎት በአንድ ወይም በሌላ መንገድ ከጋብቻ ጋር የተያያዘ ነው የሚባለው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ በተጨማሪም በኢትዮጵያ «ቤተሰብ» የሚለው ቃል የተለመደ ትርጓሜው «ቤተዘመድን» ሁሉ የሚያጠቃልል መሆኑ መታወስ ይኖርበታል፡፡ ይህም ምዕራባውያን አገሮች ካላቸው «ሁለት ተጋቢዎችንና ልጆቻቸውን ብቻ» ከሚያቅፈው ቤተሰብ በአያሌው የሚበልጥ ነው፡፡

በቤተሰብና በተለያዩ የቤተሰብ ጠቀስ ጉዳዮች ላይ **ትምህርት ልዩ ልዩ ለሆኑ ቡድኖች መሰጠት አለበት**፡፡ ይህም ለወጣቶች (አንድ ቀን ለሚያገቡ፣ ወሳኙ ጥያቄ መቼ? የሚለው ነው) ለተጫጨጩ ሰዎች፣ አዲስ ለተዳሩ ሰዎች፣  በተለያየ  ዕድሜ ለሚገኙ ባልና ሚስቶች፣ ለወላጆች፣ ለአያቶች (ከእነዚህም ብዙዎች መበለቶች ሊሆኑ ይችላሉ) ወይም ሳያገቡ ብቻቸውን ለሚኖሩ፣  ሌላው ቡድን በተለያየ የትምህርት  መስክ ለሚያገለግሉ ሠራተኞች፣ ልጆችን ለሚያሳድጉ፣ በጤና መስክ ለሚሠሩ ወዘተ ...  ናቸው፡፡

**«የቤተሰብ ሕይወት ትምህርት»** የተለያዩ የቤተ ክርስቲያን ሥራ ባሕርያትን ያጠቃልላል፡፡ ይህም «ችግርን በቅድሚያ የመከላከል» ትምህርት ሲሆን፣ በማስተማር፣ ወይም በማሠልጠን ሊደረግ ይችላል፡፡ ሆኖም «ከፈዋሽ» የምክር  አገልግሎትም ጋር ይያያዛል፡፡ ይህም ቅድመ ጋብቻ ወይም የጋብቻ ምክር አገልግሎት መሆን ይችላል፡፡  ስለዚህ **«የቤተሰብ አገልግሎት»** በዚህ መስክ፤ ተገቢ የሆነ አጠቃላይ ርእስ  ወይም መጠሪያ ነው፡፡